

**Free former judge and Ethiopian heroine Birtukan Mideksa**

# ድርጅታዊ መበስበስ፤ ጥገኝነት እና አድርባይነትን መዋጋት ያቃተው የኢህአዴግ የ«መተካካት» ድራማ

በአህመድ አባጊሣ

## ልባቸውን የናጠ ግን እንደ እባብ ያስቀጠቀጣቸው ግጥም

በውቧ የባሕር ዳር ከተማ ቀደም ባለው እና አስከፊውን የደርግ ሥርዓት መንግሎ ለመጣል በተደረገው እልህ አስጨራሽ ትግል ግንባር ቀደም ሚና ስለተጫወቱ እንደ ሙሉዓለም እጅጉ ያሉ ታጋዮች በአንድ አለብላቢ ምላስ ባለው ካድሬ አማካይነት የሰሙት ግጥም ደስ ብሏቸዋል----ወደ 1,200 የሚጠጉ በከተማዋ በሚገኘው የተንጣለለው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የመሰብሰቢያ አዳራሽ የታደሙ የንቅናቄው አባላት:: ነገር ግን ያ በአጣጣሉ፤ በቃላት አሰካኩ እና በስሜት ቆንጣጭነቱ ልክ ከወንበራቸው ጋር የተጣበቁ ያህል ድርቅ አድርጎ ያስቀራቸው ግጥም ብዙም ሳይቆይ ከገዢው የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር (ኢህአዴግ) መስራች አባል ፓርቲዎች መሀከል ትልቅ ግምት በሚሰጠው በብሔረ አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ብአዴን) ውስጥ ተንሰራፍቷል ስላለው «ሙስና»፤ «ጥገኝነት» እና «የግል ጥቅምን ብዙሀንን በድሎና ረግጦ ማራመድ» ስለተሰኙት መቅሰፍቶች አለብላቢው ግጥም አንባቢ ማውራት ሲጀምር የካድሬዎቹ ስሜት የተደበላለቀ ሆነ:: አንዳንዶች ቀድሞውንም በለመዱት

መልኩ በአመራር አባላት ምርጫ ያሸነፏቸውን እና በተለያዩ የአመራር መዋቅሮች ውስጥ ታቅፈው የነበሩ አባላቶቻቸውን ድባቅ ለመምታት ጥሩ አጋጣሚ የሚፈጥርላቸው በመሆኑ ሲደሰቱ ሌሎች ግን የንቅናቄውን እንዲሁም በአጠቃላይ ደግሞ የኢህአዴግን አካሄድ ግራ-አጋቢነት ያውቃሉና በግጥሙ የተፎከረው እነ ማን ላይ እንደሆነ በውል ስላላወቁ ያ የመገማገሚያ ሰዓት እስኪደርስ በትጥቅ ትግሉ በደርግ በግፍ የተገደሉትን ጓዶቻቸውን ረስተው ስለሚመጣው ግብግብና ስለሚንሳፈፉ አመራሮች ማሰብ ያዙ።

ዶ/ር ምሥራቅ መኮንን የተባሉት ደርባባ የንቅናቄው መስራች አባል በተለይም በዚህ ነሐሴ 29፤ 2002 በተካሄደው ስብሰባ ላይ ከታደሙ በኋላ ለምሳ ወጣ ብለው በታዋቂው የፓፒረስ ሆቴል በረንዳ ላይ ከነበሩት ከትግል አጋራቸው ከአቶ ጥላሁን ይበልጣል ጋር በመሆን ስለሚመጣው ሹም ሽር ያወጡ ያወርዱ ነበረ። የሁለቱ ወሬ ያተኮረው «የራሱን ጥቅም ለማራመድ ከከፍተኛ አመራሮች ጋር ተሞዳሙዷል» ስለሚሉት አንድ በብአዴን ውስጥ የተፈጠረ፤ የፈለጋቸውን ሰዎችም ለማዕከላዊ እና ለሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴዎች ለማስመረጥ ድርጅታዊ ሥራውን እና ተንኮሉን በሚገባ ሸርቦ መጥቷል ስላሉት ቡድን ነበረ።

«እነሱ ከእነ ጥንቅሹ ጋራ ፍሬንድ ስለሆኑ ማን ሊነካቸው? እኛ የምንላቸውና ለሕዝብ ጥቅም የሚያስቡ ሰዎችማ ሊንሳፈፉብን አይደለም እንዴ?» ይላሉ ዶ/ር ምሥራቅ በቁጭት።

ያሉትም አልቀረም ጷጉሜን 2፤ 2002 ላይ በተካሄደው ስብሰባ ሹምሽሩ ከብዙ ሙግት፤ ግልምጫ እና መጠላለፍ በግልጽ ከተካሄደ በኋላ ያ «ተሞዳሙዷል» ያሉት ቡድን 81% የሚሆኑ ያጫቸውን አባላቱን በሁለቱ መዋቅሮች ውስጥ ንቅናቄውን ወክለው ኢህኤደግ ም/ቤት ውስጥ እንዲሳተፉ በአብላጫ ድምጽ ሲረታ የእነሱ «ለሕዝብ ጥቅም የቆመ ነው» የተባለው ቡድን ግን 12.2% የሚሆን ድምጽ እንዲያገኝ ተደርጓል። ከዚህ ውስጥ ቀሪውን መቶኛ የሚሞላው ብዙዎቹ የብአዴን አባላት እንደሚስማሙበት ከሆነ «መሀል ሰፋሪ» የተባለው ቡድን ነው። ስለዚህ ጫካ እና ቆንጥሩን ስለመመንጠር፤ በኮዳ ውሃ ከ 10 ቀናት በላይ ዳገትን መግፋት፤ እንዲሁም ስለ ታንክና መትረየስ ሲወራ በትዝታ ፈረስ መንፈሳቸውን ላላ አድርገው ወደኋላ የተጓዙት አባላት በዚያች ጭብጨባን በቸሯት ግጥም አማካይነት የኋላ የኋላ ላይ እንደ እባብ ጭንቅላታቸውን ለመቀጥቀጥ፤ የቡድናቸውን አባላትም ከመዋቅር ላይ ሲወርዱባቸው ለማየት በቁ።



*(ከቀኝ ወደ ግራ) አቶ ደመቀ መኮንን (የብአዴን ሊቀመንበር)፤ አቶ ኃ/ማርያም ደሣለኝ (የደኢሕዴን ሊቀመንበር)፤ አቶ _____ _____ (የሕወሓት ሊቀመንበር) እና አቶ ዓለማየሁ አቶምሣ (የኦህዴድ ሊቀመንበር)*

## ታጥቦ ጭቃው ድርጅታዊ ጉባዔ

በ 6ኛው የኢህአዴግ ድርጅታዊ ጉባዔ በፀደቀው የግንባሩ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 18 መሠረት ግንባሩ መደበኛ ጉባዔውን ከሁለት እስከ ሁለት ዓመት ተኩል ባለው ግዜ ውስጥ እንደሚያካሂድ ተደንግጓል:: በዚህም መሠረት 8ኛው ድርጅታዊ ጉባኤ በየአባል ድርጅቶቹ (ወይንም 4ቱ ክልላዊ ሳተላይት ፓርቲዎቹ) ውስጥ ባለፈው ዓመት መጨረሻ እና በተቀበልነው አዲስ ዓመት የመጀመሪያ ቀናት ውስጥ ተካሂዷል:: በዚህ ጽሁፍ በዋናነት የማነሳቸው ጥያቄዎችም የኢህአዴግ አባላት አመራሮቻቸውን ምን ያህል በነፃነት ይመርጣሉ? ጉባዔው ጥገኝነትን ሙስናን እና አጎብዳጅነትን የቱን ያህል ለመዋጋት ቁርጠኝነት ያሳየ ነው? እንዲሁም «መተካካት» የተባለው ነገር በእርግጥ ነበረ ወይ? የሚሉትን ነው::

መሪዎችን በነፃነት መምረጥ በተባለው ጉዳይ ላይ አባላቱ ራሳቸው በየኮሪደሩ፤ በየጓዳው እና በየሥርቻው ሲናገሩ እንደተደመጠው ቀርቦ እና ተዘጋጅቶ የመጣላቸውን በአብላጫ ድምጽ ለይስሙላ ክርክር አድርገው ግን በትግሉ የቆዩ እና አባል ፓርቲውን በዋናነት በሚመሩ ሰዎች ይሁኝታ የሚሰጠውን እያንገራገሩም ቢሆን በትንሽ ተቃውሞ ከመምረጥ አልዳኑም:: ይኼ ደግሞ ዴሞክራሲያዊ አሠራርን የተከተለ ሳይሆን የ «እኔ አውቅልሀለሁ» ሥርዓትን በአባላቱ ላይ ለመጫን ያለመ አምባገነናዊ አካሄድ ነው:: ለምሳሌም ከአባል ፓርቲዎቹ አንዱ በሆነው የኦሮሞ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ድርጅት (ኦሕዴድ) በአዳማ ከተማ ጳጉሜን 2 እና 3 በተካሄደው ግምገማ ላይ አሁንም ተስፋ ያልቆረጡ አባላት በሙስና እንደተጨማለቁ ከእነ ማስረጃው ጭምር በማረጋገጥ ሊያወርዷቸው የሚችሉ የመሰሏቸው አንዳንድ የአመራር አባላቶቻቸው ላይ ያዙኝ ልቀቁኝ የማለት ያህል የግምገማ ዶፍ ቢያዘንቡባቸውም ድርጅቱ ግን

በኢህአዴግ መሪዎች የቀረበለትን አማራጭ ከመተግበር እና ከአሸከርነት ያለፈ ምንም ሚና ሊኖረው ስለማይችል እነሱ እያለቀሱ እና እየተንጨረጨሩም ቢሆን «ከምክር እና ከተግሳጽ በኋላ»፤ «ለድርጅቱ ባላቸው ታማኝነት እና በፀረ ሰላሞች ላይ በሚደረገው ትግል ቁርጠኝነታቸው ከቶም የማይጠየቅ ስለሆነ» በሚል የግምገማ ማጠቃለያ ብዙሀን እያዩ ለማዕከላዊና ለሥራ አስፈፃሚ አስመርጧቸዋል:: በመሆኑም ብዙዎች እንደሚስማሙበት ነፃነት የሚባለው የአመራር ምርጫ ሂደት በኦህዴድ ከዚያም ስንለጥጠው በኢህአዴግ ውስጥ ልክ ፍፁም ርቆ እንደተቀመጠ ዳቦ ያህል የማይገኝ ሆኗል::

## ድርጅታዊ መተሳሰርና መሳሳብ፤ አድርባይነት እና ሙስና

ለግንባሩ ውስጣዊ አሠራር ቅርበት ያላቸው ምንጮቼ እንደነገሩኝ ከሆነ በግንባሩ ውስጥ ተተክለው ያደጉ በርካታ አሉታዊ ባሕሎችና አሠራሮች በመኖራቸው «መተካካት» የሚባለው ነገር እንዲህ በቀላሉ የማይሳካ ነው:: ከእነዚህ አሉታዊ ባሕሎች አንዱ ደግሞ በግንባሩ እና በቢሮክራሲያዊ መዋቅሩ የኃላፊነት ቦታ ላይ የተቀመጡ እና «በድርጅቱ ውስጥ የተሻለ ተቀባይነት አለን»፤ «ድርጅቱን ታግለን ለዚህ ለደረሰበት አብቅተነዋል» የሚል ትምክህተኛ አመለካከት ያላቸው ቱባ ካድሬዎች የሚፈጥሩት የጥቅም ወይንም የትስስር ቡድን መሳሳብ አዝማሚያ ነው:: ይህ አሉታዊ ባሕልም ከቅርብ ግዜ ወዲህ የግንባሩን ሕልውና የመፈታተን አቅም የያዘ መሆኑ ሲነገርለት የቆየ እና በድርጅቱ ውስጥ ከሚታየው የቡድንተኝነት ስሜት (ወይንም የኔትወርክ ምስረታ) ጋር በእጅጉ የተቆራኘ ነው::

እናም የግንባሩ ዓይነተኛ መለያ በሆነው የዴሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት መርህና acclamation የሹመት አሠራር መሠረት አንድ የድርጅቱ አባል በአመራር ቦታ ላይ ለመቀመጥ በደረጃው ካሉ የአድራጊ ፈጣሪነት ስልጣን ከያዙና «ኮር» የሚባሉትን ጥቂት «ታማኝ» ግለሰቦች ይሁኝታ ማግኘት አለበት:: እነዚህ የኮር አመራር አባላት ደግሞ ግለሰቡን በግል ስሜታቸው ላይ ተመስርተው ሊጠቅሙትም ሆነ ሊጎዱት ሙሉ ስልጣን ያላቸው ናቸው:: ለዚህም ሲባል እነዚህ የ «ኮር» አመራር አባላት ሊያገልሉት የሚፈልጉትን ግለሰብ ከሚገባው ወይንም ከሚመጥነው ቦታ እና ደረጃ በታች በማስቀመጥ አልያም ከእነ ጭራሹ በማስወገድ የሚፈልጉትን ሰው ይተኩበታል:: ይህም አሠራር በሁሉም አባላት ዘንድ የሚታወቅ በመሆኑ የስልጣን ቦታ ላይ ለመቀመጥ ወይንም ለመሾም የሚፈልግ አንድ የድርጅቱ አባል «ኮር» በሚባሉት አባላት ዘንድ ተቀባይነት ለማግኘት ሲል አላስፈላጊ ወይንም የማይገባ ባሕሪ ማሳየት ወይንም ስብዕናውን የሚጉዱ ተግባራትን ለመፈፀም ይገደዳል::

ከዚህ ሥር ከሰደደው አሉታዊ ባሕል በተጨማሪም በግንባሩ ውስጥ ጠንከር ባለ መንገድ እየተገለፀ እና በርካቶች እንደሚስማሙበት የግንባሩን ተአማኒነት በእጅጉ ሊጎዳው የሚችል ሆኖ ብቅ ያለው ሌላ ባሕል ደግሞ የአድርባይነት ችግር ነው፡፡ ይህ ችግር ከአባል ፓርቲዎቹ አንዱ በሆነው እና ቀደም ብለን በመግቢያችን ላይ ባየነው ብአዴን ስብሰባ ላይ በስፋት ተንፀባርቋል፡፡ ንቅናቄው በአስከፊ የአድርባይነት ችግር ውስጥ ተዘፍቆ የመገኘቱ ጉዳይ በስብሰባው ላይ ፕሬዚዲየሙ ላይ ተሰይመው ለነበሩ ቱባ ባለስልጣናት በጥያቄ መልክ ቀርቦ ውይይት እንደተደረገበት በስብሰባው ተሳታፊ የነበሩ ምንጮቼ ገልፀውልኛል፡፡

የመንግሥት ኮምዩኒኬሽን ጉዳዮች ሚ/ር እና የብአዴን ከፍተኛ አመራር አባል የአድርባይነት ችግር እየተስፋፋ እንደሚገኝ ከብአዴን አልፈው የሌሎችን አባል ፓርቲዎች ልምድና ተሞክሮ በመጥቀስ አምነዋል፡፡ የችግሩን መስፋፋት ማመናቸውን የምንቀበለው እና እንደ በጎ አካሄድ የምንቆጥረው ቢሆንም ለይምሰል እንኳ ብአዴን ይህንን ችግር ለመቅረፍ ምን ማድረግ እንዳለበት አለመግለፃቸው ብሎም በዚህ ጉባዔ ላይ በተደረገው መፈጠርን የሚያስጠላ የሚመስል ግምገማ ላይ እንኳ እንደ መስፈርት አለመነሳቱ የእሳቸውን ጨምሮ የሌሎች የንቅናቄው «ኮር» አመራር አባላትን መበስበስ ብሎም ቁርጠኝነት ማነስ ያመላከተ ነው፡፡ እኒህ ሰው በለመዱት የስብሰባ ላይ መተጣጠፍና አድበስብሶ የማለፍ ዘዴ በመጠቀም ጭራሽ አድርባይነት በሥርዓት ደረጃ ተቋማዊ ቅርጽ ይዞ የወጣ በመሆኑ በአጭር ግዜ ውስጥ ወይንም በቀላሉ ለማስወገድ የሚከብድ መሆኑን ብቻ ለማመን የፈለጉ መስለው ታይተዋል፡፡

ያለው አባተ የተባሉ የስብሰባው ተሳታፊ አባል በጉዳዩ ላይ ጥያቄ ባቀረቡበት ወቅት፤

> «ከብቃትና ችሎታ ይልቅ ራስን ዝቅ አድርጎና ያልተገባ አጎብዳጅነት ባሕሪን በማሳየት ስብዕናን በመሸጥ ራስን የመደበቅ ተግባር ነው፡፡ ዋና ዓላማውም ያለሙትን የስልጣን ቦታ ለማግኘት የመሞከር አዝማሚያ ነው፡፡ ለመሆኑ ይኼንን አደገኛ አዝማሚያ እንዴት ልንዋጋው እንችላለን?»
>
> **(አቶ ያለው አባተ፤ የብአዴን ድርጅታዊ ስብሰባ ላይ ነሐሴ 29፤ 2002 በጧቱ ክፍለ ግዜ ከተናገሩት ላይ የተወሰደ)**

ብለው ነበረ፡፡ ግና ምን ዋጋ አለው? የመንግሥት ኮምዩኒኬሽን ጉዳዮች ሚኒስትሩ ምላሽ ግን ለዚህ ጥያቄ ተገቢውን ምላሽ ለመስጠት ያልፈለገም ያቃተውም ጭምር ሆነ!

ማንም ለድርጅቱ የቀረበ ሰው እንደሚገነዘበው በግንባሩም ሆነ በተለያዩ የከተማ እና የገጠር አካባቢዎች ያሉ መንግሥታዊ ስልጣኖች የሚያዙት ግልጽ በሆነ መስፈርት ወይንም እነሱ እንደሚሉት «የሐሳብ መተጋገል ተደርጎ» ሳይሆን ከላይ ወደ ታች በተዘረጋ ኔት ወርክ አማካይነት በሚንሽራሽር የወሬ እና የአሉባልታ ቅብብሎሽ ላይ የተመሠረተ በመሆኑ፤ ዕውቀት፤ ክህሎትና የትምህርት ዝግጅት በስልጣን ድልድሉ ያላቸው ቦታ ከግዜ ወደ ግዜ እየወረደ የመጣበት ሁኔታ ነው ያለው፡፡

በሌላ በኩል ሙስና ኢህአዴግ መኖሩን ለማመን ከፈለገበትም ሆነ በስልጣኑ የመጡበትን የገዛ ነባር መስራች አባላቱን ጭምር ለመምታት በይፋ ከተጠቀመበት ግዜም በፊት የነበረ ለመሆኑ አሁንም የግንባሩ የኋላ ታሪኮች ብሎም ቅርበት ያላቸው አባላቱ ይናገራሉ፡፡ ይህ የአገርን ሀብት ለጥቂት በኔትወርክ ለተሳሰሩ ደም መጣጮች የመስጠትና ሐገሪቷን እና የድሀውን የኢትዮጵያን ሕዝብ በተመጽዋችነት ራቁቱን በማስቀረት የራስን ጥቅም ማግበስበስን የሚያስብ አሠራር ዋናው ችግሩ ግን ባለስልጣናቱ ከሚናገሩት ፍፁም የተለየ ነው፡፡ ለምሳሌም በዋናው የኢህአዴግ 8ኛ ድርጅታዊ ጉባዔ ማጠናቀቂያ ወቅት በድጋሚ የግንበሩ ሊቀመንበር በመሆን የተመረጡት እና የአገሪቱ ጠ/ሚኒስትር አዲስ አበባን በምሳሌነት በመውሰድ ለአባላቶቻቸውና ለተጋባዥ እንግዶች፤

> ‹‹ሙስናን በተመለከተ ታች ያለውን እየነካካችሁ ላያችሁን ትታችኋል ለተባለው፣ ታቹንም ባለመተው ላዩንም መጥረግ ነው፤ እንደ መነሻ የወሰድነው በምርጫ ወቅት የአዲስ አበባ ሕዝብ የነገረንን ነው፡፡ በምርጫው የመረጠንም ያልመረጠንም የአዲስ አበባ ሕዝብ በዝቅተኛ የአመራር አካላት ከፍተኛ ብልሽት አለ ብሎናል፡፡ ይህ ሕዝብ ያነሳውን ጥያቄ እኛ በራሳችን መረጃ ላይ ተመስርተን ውድቅ ልናደርገው አይገባም፡፡ ሕዝቡ ካነሳው በእርግጥ መኖር አለመኖሩን እንፈትሸው

አልን፡፡ ልንፈትሸው የምንችለው በግምገማ ነው፡፡ ከምርጫው በኋላ የተወሰነ ዝግጅት አድርገን የወረዳ መዋቅሮችን ወደ መገምገምና ወደ መፈተሽ ነው የገባነው፡፡ ምክንያቱም ኅብረተሰቡ ችግሩን ጎላ ባለ መልኩ ያነሳው በዚህ አካባቢ በመሆኑ ነው፡፡ ምናልባት በግምገማው አደገኛ የሙስና ጉዳይ አላገኘንም፤ እዚህም እዚያም 1000 ብርና 2000 ብር ዝርፊያ ሊኖር ይችላል፡፡ ነገር ግን አንድ ሺሕ ብር መስረቅ፣ አንድ ሚሊዮን ብር የመስረቅ ያህል ባይሆንም ያው መስረቅ ነው፡፡ መወገዝና መወገድ አለበት፡፡ ሁለተኛ ከሙስና በላይ በዝቅተኛ መዋቅሮች የመልካም አስተዳደር መጓደል አለ፡፡ ከሙስና በላይ ሰፋ ብሎ የታየው እሱ ነው፡፡ እነዚህን ሁለቱን የማስተካከል ጥረት አድርገናል፡፡ ነገር ግን በክፍለ ከተማ ይህ ችግር የለም የሚል ድምዳሜ የለም፡፡ ስለዚህ መረጃው ወደ ወሰደን ያለማመንታት እንሄዳለን፡፡ ወደ ክፍለ ከተማ ከወሰደን መረጃውን ተከትለን እንሄዳለን፡፡ ከክፍለ ከተማ አልፎ ወደ ፌዴራል ከወሰደን እንሄዳን፡፡ በየትኛውም ደረጃ ከሙስና ነፃ የሆነ መዋቅር አለን ብለን አልደመደምንም ከወረዳና ከክፍለ ከተማ ያገኘነው መረጃ አልፎ አልፎ ወደ ከተማ የወሰደን አለ፡፡ ለምሳሌ ወደ መሬት አስተዳደር የወሰደን አለ፡፡ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ቋቶች አሉ፡፡ ነገር ግን ከውጭ እንደሰማነው በጣም ስፋት ያለው አይደለም፡፡ መረጃ ባገኘን ጊዜ ወደየትኛውም መዋቅሮቻችን እንሄዳለን፡፡››

**(ጠ/ሚ ______ _______ በአዳማ ከተማ በተካሄደው የኢህአዴግ ድርጅታዊ ጉባዔ ላይ ከተናገሩት የተወሰደ)**

በማለት የሰጡት ምላሽ ባንድ በኩል መቼም ቢሆን የማያመልጡት በከፍተኛ የአመራር ደረጃ የሚፈፀምን ሙስና የመዋጋት ጥያቄ ሲመጣ ወደራሳቸው እንዳይላከክ ለመከላከል የሚያደርጉትን አይን ያወጣ መፍጨርጨር ብሎም እየዋሸሁ ዘላለም እኖራለሁ የሚለውን ትምክህታቸውን ፍንትው አድርጎ ያሳየ ነው፡፡ የአዲስ አበባም ሆነ የሌላው ክልል ሕዝብ ትልቁ ጥያቄው በዝቅተኛ የአመራር እርከኖች የሚፈፀሙ ሙስናዎች ላይ ሊሆን አይችልም፡፡ ዝሆኖችን ትቶ አይጦችን ብቻ እየመረጠ ለይምሰልና ተቀናቃኙን ለማስወገድ ሲባል የሚመታን የበሰበሰ አመራር የኢትዮጵያ ሕዝብ ከላይ ታች አምርሮ እንደሚቃወመው እየታወቀ ይኼን ዓይነቱን ቆሻሻ እና ሐፍረተ ቢስ ንግግር ማድረግ አሁንም ቢሆን ግንባሩ በሙስና የተጨመላለቁና የአገሪቱን አንጡረ ሐብት ከሕዝቧ ጉሮሮ ብሎም በቢልዮኖች ዶላር የሚቆጠር የእርዳታ ገንዘብን ደግሞ ከግብር ከፋዩ በውጭ መንግሥታት አማካይነት በመንጠቅ በልተው የማይጠግቡ ጆቦቻቸውን ይዘው በስልጣን ለመቀጠል ያላቸውን ቁርጠኝነት ያሳየ ነው፡፡ በሌላ በኩል በአዲስ አበባ በሚገኙት 10 ክፍለ ከተሞች ላይ የተነሳው በሙስና የተያያዘ ጥገኛ አመራር ሕዝቡ በሰጠው ጥቆማ እና ቅሬታ ላይ ተጋንኗል እንደተባለው አይደለም፡፡ እጅግ እጅግ በጣም ሕዝቡ ካለው በላይም ዘልቆ የሚገኝ ነው፡፡ እኔ የማውቃቸውን ሶስቱን ብቻ ጠቅሼ ወደሚቀጥለው ርዕስ ልሸጋገር፡፡



*የአዳማው የኢህአዴግ 8ኛ ድርጅታዊ ጉባዔ ተሳታፊዎች በከፊል*

ሶስት በአዲስ አበባ የሚገኙ የመንግሥት መ/ቤቶች ተገቢ ማስረጃ ሳይዙ 877.5 ሚሊዮን ብር ያለአግባብ ክፍያ ፈጽመዋል፡፡ በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ግልጽ ጨረታ ሳይወጣ የ22.4 ሚሊዮን ብር ግዢ ተፈጽሟል ፡፡በተመሳሳይም በአራዳ ክፍለ ከተማ ጨረታ ሳይወጣ ከአንድ ኩባንያ የ10.8 ሚሊዮን ብር ግዢ ተፈጽሟል፡፡ ይኼም አነሰ ከተባለ በውኃና ፍሳሽ ባለሥልጣን ተቀጣሪ የሆኑ 13 ሠራተኞች 8.9 ሚሊዮን ብር አጉድለዋል፡፡ እንግዲህ እኔ አንድ ግለሰብ ነኝ፡፡ ይኼንን በአጋጣሚ ከምንጮቼ ከነማስረጃው ነው በእጄ ያስገባሁት፡፡ ግን እኔ ያልሰማሁት ሌላ ስንት

ይኖራል? በእርግጥም ብዙ ይኖራል። እና ይኼ ሁሉ ዓይን ያወጣ ዘረፋ ባለበት ሁኔታ ነው ጠ/ሚኒስትሩ ለዚያውም ብዙ አባላቶቻቸው አንድ ቁርጥ ያለ ሳይኖኛውን አመራር ይመታል የተባለ እርምጃ ሲጠብቁ እሳቸው ግን በዝቅተኛው አመራር ደረጃ እንኳ «እዚህ እና እዚያ 1000 ወይ 2000 ብር ሊኖር ይችላል» ብለው ጉዳዩን በማዋረድና በማቃለል የሚያቀርቡት።

## የመቀያየርን ማጨናበርና «መተካካት»ን ምን አገናኛቸው?

ኢህአዴግ ዘንድሮ በአባል ፓርቲዎቹ ከዚያም በራሱ ውስጥ ባካሄዳቸው ጉባዔዎች እንደተለመደው «ምን ቁም ነገር ያዙና ነው የሚለፈልፉብን?» ብሎ ሕዝብ እንዳይወርፈውና ተዓማኒነት እንዳያጣ አስቦ ይመስላል «መተካካት» የሚል አዲስ ቃል ይዞ ብቅ ብሏል። ለነገሩ መተካካት የሚለው ቃል ባሳለፍነው ዓመት መጨረሻ እና በአዲሱ የ 2003 ዓ.ም የኢህአዴግ ፊሽካ መንፊያ እና የድራማ ርዕስ ሆኖ ይምጣ እንጂ መጀመሪያ ግን ልክ 2002 ሲጀመር መስከረም 7 ላይ ጠ/ሚኒስትሩ ለአገር ውስጥና ለውጭ የፕሬሱ አባላት በጽሕፈት ቤታቸው በሰጡት መግለጫ ላይ «የዱላ ቅብብሎሽ» በማለት ያመላከቱት ጉዳይ ነው። በዚያው መግለጫ ላይም ረዘም ላለ ግዜ ከፓርቲው ጋራ በተለይም ከትጥቅ ትግሉ ጋራ የቆዩ አመራር አባላትን በቀጣዮቹ 5 ዓመታት በሶስት ዙሮች ደረጃ በደረጃ በወጣትና ትኩስ በሆኑ አዳዲስ የአመራር አባላት የመተካት ሂደት እንደሚኖር ገልፀዋል።

ጠ/ሚኒስትሩ እንዳመለከቱት ከሆነ የግንባሩን የልማት፤ የሰላምና የዴሞክራሲ መርሆዎች በሚገባ የተረዱ እና ከነባር አመራር አባላት ልምድን በተገቢው መንገድ የቀሰሙ ተተኪዎች የተጀመረውን የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ሂደት ዱላ በቅብብል መልክ ከአመራሩ በ 5 ዓመት ግዜ ውስጥ በመረከብ እነሱ ደግሞ በየመዋቅሩ ለሕዝቡ ያደርሳሉ። ይኼ መቼም ተራ የቁጭ በሉ ማታለያ መሆኑን በወቅቱ ሰፋ ባለው ጽሁፌ ገልፄዋለሁ፤ ብዙዎች የኢትዮጵያን የፖለቲካ ሁኔታ በቅርበት የሚከታተሉ ታዛቢዎችም ጭምር እውነትነቱን ተጠራጥረው ጽፈዋል። ያ መግለጫ በተሰጠ በ 1 ዓመት ግዜ ውስጥ የ «መተካካት» ጨዋታው ለፈተና በተለይም በየአባል ፓርቲዎቹ ጉባኤ ውስጥ ቀርቦ የተገኘውን ውጤት ስናይ ቀድሞውኑ ያልነውን ያንፀባረቀ ሆኗል።

ይህ የ‹መተካከት› አካሄድ በቅን ልቦና ስለመካሄዱ በእጅጉ ከሚጠራጠሩ አንዱ መሆኔን አስረግጬ ልገልጽ እወዳለሁ። በመጀመሪያ ደረጃ ከተወሰኑ ሰዎች በስተቀር አንጋፋዎች የኢሕአዴግ

ባለሥልጣናት የድርጅቱ ሥራ አስፈጻሚ አባላት ናቸው፡፡ ከእነዚህ ሰዎች ውስጥ የተወሰኑት ወደ መንግሥት ሥልጣን የመምጣት ፍላጎት የላቸውም፡፡ የጤና ጉዳይ በአንዳንዶቹ ዘንድ ጎልቶ ሊጠቀስ ይችላል፡፡ የዕድሜ ጉዳይም በሌሎቹ ላይ እንዲሁ፡፡ ጥቂቶች ግን ከነዚያም ጉዳዮች በላይ ያላቸውን የልዩነት ሐሳብ ይዘው ከግንባሩ ጋር መቀጠል ባለመቻላቸውና ተስፋ በመቁረጣቸው ነው ለመውጣት ቀድሞውኑም ማመልከቻቸውን ያስገቡት፡፡ ጥቂቶች ደግሞ ሲያወሩ ምናልባት በሚቀጥሉት ወራቶች የፌዴራል ሥነ ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን የባለሥልጣናት ሀብት ምዝገባ አካሂዳለሁ በማለቱ እዚህ ፈተና ውስጥ ላለመግባትም ይሆናል በማለት ጨምረው ምክንያታቸውን ያስረዳሉ፡፡

አንዳንድ ግዜ ለ «መተካካት» የሚሰጠውና የሚደረደረው ምክንያት ደግሞ ለራሳቸው ለኢህአዴግ አባላትም የሚዋጥ አይደለም፡፡ ጷጉሜን 4 ቀን 2002 በሐዋሳ ከተማ በተካሄደው የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ደኢሕዴን) ጉባዔ ላይ አምባሳደር ተሾመ ቶጋ ለተሰብሳቢው፤

> «በትጥቅ ትግል ውስጥ የተሳተፉ አንጋፋ ጓዶች እንዲለቁ ይደረጋሉ፡፡ ድርጅታቸው ይህን ማድረጉ ለድርጅቱ ብቃትና ቀጣይነት ጠቃሚ ሆኖ በመገኘቱ ነው፡፡ ‹‹በዚህ ደረጃ ወደ ጎንም ወደ ላይም የሚወጡ ተተኪዎች ብቃትን በማሳደግ ሒደት ላይ ነን፤»
>
> **(አምባሳደር ተሾመ ቶጋ በሐዋሣ ከተማ ላይ ጷጉሜን 4፤ 2002 ለደኢሕዴን አባላት ከተናገሩት የተወሰደ፤ ቃለ ጉባዔ ላይ የሠፈረ)**

ብለው መናገራቸውን ተከትሎ የክልሉ ም/ቤት መሰብሰቢያ አዳራሽ ገና እግራቸው ወጣ ሳይል አንዳንድ በቡድን በቡድን ሆነው ሲያወሩ የነበሩ ካድሬዎች፤ «ምነው እውነቱን ቢነግሩን?» ሲሉ እንዳደመጡ ሁለት የስብሰባው ተሳታፊዎች ገልፀውልኛል፡፡ ተተኪ የሚባል አንድ የሚያውቁት ሰው እንኳ ንቅናቄውን ወክሎ በስራ አስፈፃሚነት ወደ ኢህአዴግ ም/ቤት

ባልሄደበት ሁኔታ አባላቱ ስለ ድርጅታቸው ቀጣይነት እና ብቃት ማሰብ ሲሳናቸው ነው የታየው::

በጽሁፌ ላይ አመራሩ ነባሮቹን ቱባ አባላቱን የመተካት ቁርጠኝነት እምብዛም እንዳላሳየ፤ ይልቅ የመተካካት ድራማው የይምሰል መሆኑን እና ሌላ የፖለቲካ ጨዋታ ለማሳካት እንደተጠቀመበት እንዲሁም በመጨረሻው እና በአዳማ ከተማ በተካሄደው የኢህአዴግ ጉባዔ ላይ በወጣው አቋም መግለጫ ላይ ታጥቦ ጭቃነት እና መበስበስ በግልጽ እንደታየ ለማንጸባረቅ እሞክራለሁ::

በቅድሚያ በነዚህ ጉባዔዎች ላይ ኢህአዴግ አዳዲስ ተተኪ አመራር አባላትን አላመጣም ለሚለው መከራከሪያዬ የየአባላት ፓርቲዎቹን የመጨረሻ የሥራ አስፈፃሚ አባላት ምርጫ በማስረጃነት እጠቅሳለሁ:: የኢህአዴግ ማዕከላዊ ኮሚቴ በወሰነው እና በሕገ ደምቡ አንቀጽ 18 ንዑስ አንቀጽ 3 ላይ እንደሰፈረው የኢህአዴግ አባል ፓርቲዎች ለኢህአዴግ ሥራ አስፈፃሚ እና ማዕከላዊ ኮሚቴ በአባላትነት የሚሳተፉ የአመራር አባላቶቻቸውን ይመርጣሉ:: በዚህም መሠረት የኢህአዴግ አስኳል ፓርቲ መሆኑ የሚታመንለት እና የትጥቅ ትግሉን አህዱ ብሎ በመጀመር ዳር ያደረሰው [የሕዝባዉ ወያኔ ሓርነት ትግራይ (ሕወሓት)] ጿጉሜን 3 ቀን በመቐለ ከተማ ባካሄደው ጉባዔ ላይ ሕወሓትን ወክለው በሥራ አስፈፃሚ እና በማዕከላዊ ኮሚቴ አባልነት በኢህአዴግ መዋቅር ውስጥ የሚሳተፉ አመራር አባላቱን በምስጢር የድምጽ አሰጣጥ ሂደት መርጧል፡፡ በዚህ የድምጽ አሰጣጥ ሂደት መሠረትም በመጨረሻ ለሥራ አስፈፃሚነት፤

1. አቶ ______ _______ (ጠ/ሚኒስትሩ)

2. አቶ ፀጋዬ በርኸ

3. አቶ አባዲ ዘሞ

4. አቶ አባይ ወልዱ

5. ወ/ሮ አዜብ መስፍን

6. ዶ/ር ቴዎድሮስ አድኻኖም

7. አቶ ቴዎድሮስ ሐጎስ

8. አቶ ደ/ጽዮን ገ/ሚካኤል

9. አቶ በየነ ምክሩ

የተባሉ ነባር አባላቱን በሥራ አስፈፃሚነት መርጧል:: በዚህ አሳፋሪ ሂደትም ሕወሓት ለመተካካት ያለውን አናሳ ዝግጅት እና ቁርጠኝነት አረጋግጧል:: ሕወሓት የሠራው ድራማ ምናልባትም በብአዴን ካልሆነ በሌሎቹ ያልታየ ዓይነት ነው:: በሕወሓት በኩል ሆነው ኢህአዴግን እንደ እንዝርት በማሾር እንዲሁም በነፍስ አባትነት የሚታወቁት አቶ ስብሐት ነጋ (አቦይ ስብሐት) ቀደም ብለው «በገዛ ፈቃዳቸው» በፓርቲው አመራር አባልነት መቀጠል እንደማይፈልጉ ተናግረው ተሸኝተዋል:: በተመሳሳይም ከኢትዮ-ኤርትራ የድንበር ግጭት በኋላ ለኢትዮጵያ ያልተገኘን መሬት እንደተገኘ አድርጎ ገልብጦ የድንበር ኮሚሽኑን ውሳኔ በማንበብ የሚታወቁት እና በከፍተኛ የአገር ክህደት መጠየቅ የሚገባቸው አቶ ስዩም መስፍን እንዲሁ ከዚህ ምርጫ ቀናት ቀደም ብለው «ልቀቁኝ» ብለው ተለቀዋል:: በተመሣሣይም ዶ/ር ገብረአብ በርናባስና ዶ/ር ኃይለሚካኤል አበራ እንዲሁ ከከፍተኛ አመራር አባልነት ለመነሳት አስቀድመው ጠይቀው የተፈቀደላቸው እና በምርጫ ሳይሆን ራሳቸው በፈለጉ ግዜ የለቀቁ አባላት ሆነዋል:: ስለዚህ ምርጫው የይስሙላ ነው:: የኢህአዴግ መሪዎች በሕዝባዊው ብቻ ሳይሆን በራሳቸው ድርጅታዊ ምርጫም መሸነፍን አጥብቀው ስለሚጠሉና ስለማይቀበሉ «ስለበቃኝ ትቻለሁ» በሚል ድራማ ገሸሽ ማለቱን መረጡ:: የሆነው ሆኖ ከተመረጡት 9 አባላት አንድም ቀደም ሲል በሕወሓት ማዕከላይ ኮሚቴ ውስጥ ያልነበረ ባለመኖሩና ሌሎቹ ደግሞ ጭራሽ የአገሪቱ አድራጊ ፈጣሪ በመሆን የሚታወቁ ስለሆኑ መተካካትን አሽቀንጥሮ የጣለ የአምባገነኖችን ሐሳብ በምስኪኑ የትግራይ ሕዝብ ላይ መልሶ የጫነ ስብሰባና «ምርጫ» ሆኖ አልፏል::



*ከግራ ወደቀኝ አቶ ____ _____፣ አቶ ፀጋዬ በርኸ፣ ዶ/ር ቴዎድሮስ አድኻኖም እና ወ/ሮ አዜብ መስፍን*

አቶ_____ ______አድራጊ ፈጣሪና ቁንጮ ስለሆኑ እንተዋቸው:: ባለቤታቸው ወ/ሮ አዜብ መስፍን በሹም ሽሮችና በፖለቲካ ሽኩቻዎች ጭምር የተሳተፉ ሳጥናኤላዊ ባሕሪን የተላበሱ ሴት ናቸው:: ላለፉት 19 ዓመታት በግንባሩ ውስጥ ዋና ቦታ ይዘው ቀጥለዋል:: አቶ አባይ ወልዱ በትጥቅ ትግሉም የነበሩ፣ በማይረሳው የሕወሓት ክፍፍል ወቅት ቴክኒካል አሬንጅመንት ተብሎ የቀረበውን የእነ አሜሪካን ሉዓላዊነታችንን የደፈረ ቆሻሻ ሰነድ ጠ/ሚኒስትሩንና ጥቂቶችን ተከትለው ሳያላምጡ የዋጡ ነባር አባል ናቸው:: ዶ/ር ቴዎድሮስ አድኻኖም ላለፉት 5 ዓመታት የጤና ጥበቃ ሚኒስትር ሆነው ያገለገሉ ስለሆኑ አዲስ ሊባሉ የማይችሉ ናቸው:: የአቶ ፀጋዬ በርኸ ዳግም ምርጫም የክልሉ ፕሬዚዳንትነት ሚናቸው ሊቀጥል እንደሚችል ያመላከተ ሆኗል:: ነባር አባል መሆናቸውን መላው የትግራይ ሕዝብ ያውቃል:: አቶ ቴዎድሮስ ሐጎስን ማን የማያውቅ አለ? «አፍንጫ ሲነካ. . .» እንዲሉ እነ ስዩም ሲከፋቸው ቀድመው የሚያለቅሱ፣ በየድረገፁ በዘረኛ እና ቀፋፊ ስድባቸው ያሰለቹ ባለጌ ፖለቲከኛ ናቸው:: አቶ ደብረፅዮን ገ/ሚካኤል በቴሌ መዋቅር ውስጥ ሆነው ስንቱን ሕገወጥ ጫረታ በመስጠት የአገር ሐብትን ለማውደም በተደረገው ጥረት ግንባር ቀደም እንደሆኑ ይታወቃል:: የሕወሓት ማዕከላዊ ኮሚቴ አባላትን ዝርዝር ከ 1984 ጀምሮ ስመለከተው እሳቸውን ብዙ ግዜ በተለይም ከ 1992 በኋላ አግኝቻቸዋለሁ:: አቶ አባዲ ዘሞ በበረሐው የሙሴ ግድያ እንዲሁም በሌሎች በርካታ የጠ/ሚኒስትሩ ቡድን ተጠያቂ በሚሆንባቸው ግድያዎች ቀጥተኛ ተሳትፎ ያላቸው ነባር የሕወሓት አባል ናቸው:: አቶ በየነ ምክሩም በበርካታ የመንግሥትና የፓርቲ ድርጅቶች ውስጥ ላለፉት 18 ዓመታት ያገለገሉ ነባር አባል ናቸው:: ሕወሓት በዚህ አሳፋሪ አካሄዱ በመቀጠል አቶ _____ ______ን በድጋሚ በሊቀመንበርነት መርጧል::

በሁለተኛ ደረጃ ኢህአዴግን እንደ አንዳንድ ነባር የፖለቲካ ተንታኞች ምሳሌ ልክ አራት ሰዎች እንደተቀመጡባት ትንሽ የቤት አውቶሞቢል ብንመስለው ጋቢና በመቀመጥ ይታወቅ ወደነበረው የብሔረ አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ብአዴን) እንሂድ፡፡ በእርግጥ ብአዴን አሁን አሁን ያንን የጋቢና ቦታውን መነጠቁን የኢህአዴግ ጉባዔ በገሀድ አሳይቶናል፡፡ የታኮነት ሚናውን የተነጠቀው ብአዴንም ቀደም ባለው በባሕር ዳር ስብሰባው ባደረገው የከፍተኛ አመራር አባላት ምርጫ ንቅናቄውን ወክለው በኢህአዴግ ም/ቤት ውስጥ የሚሳተፉ የማዕከላዊ ኮሚቴ አመራር አባላቱን መርጧል፡፡ ከእነዚህ አባላቱ ውስጥም የሚከተሉትን 9 አባላት ወደ ሥራ አስፈፃሚው አምጥቷል፤

1. አቶ አዲሱ ለገሠ
2. አቶ ገዱ አንዳርጋቸው
3. አቶ ደመቀ መኮንን
4. አቶ አያሌው ጎበዜ
5. አቶ ብርሐን ኃይሉ
6. አቶ ተፈራ ደርበው
7. አቶ ካሣ ተ/ብርሐን
8. አቶ ብናልፍ አንዱዓለም
9. አቶ ____ ______ (የመንግሥት ኮምዩኒኬሽን ጉዳዮች ሚ/ር)

የብአዴንን ዝርዝር ስንመለከት ከሕወሓት ጥቂት የተሻለ ነገር ማግኘታችን እንዳለ ሆኖ ግን በጥቅሉ ሲታይ ብአዴንም በአብዛኛው ነባር የአመራር አባላቱን በአዳዲስና ከዚህ ቀደም ሕዝብ በማያውቃቸው ሰዎች የመተካት ሂደትን ብዙም አላሟላም::



*ከግራ ወደ ቀኝ አቶ ____ _____፣ አቶ አዲሱ ለገሠ፣ አቶ አያሌው ጎበዜ፣*

*አቶ ደመቀ መኮንን እና አቶ ተፈራ ደርበው*

የመንግሥት ኮምዩኒኬሽንስ ጉዳዮች ሚ/ሩ ከትጥቅ ትግሉ ግዜ ጀምሮ የነበሩ እንዲያውም ኢህአዴግን ከጠ/ሚኒስትሩ ጎን በመሆን የሚያሾሩ በመሆን የሚታወቁ ኤርትራዊ «አማራ» ናቸው:: አቶ ተፈራ ደርበው የፌዴራል ግብርናና ገጠር ልማት ሚ/ር በመሆን ለዓመታት ስለሚታወቁ በምንም መስፈርት አዲስ አመራር አይደሉም:: ግለሰቡ በተለይ በምርጫ 2002 ከተቃዋሚዎች የመጣባቸውን የመርህ፤ የአይዲኦሎጂ እና የፖሊሲ ጥያቄ ለመመለስ በመቸገር የሚታወቁ ብቃት የለሽ አመራር አባል ናቸው:: አቶ ብርሐን ኃይሉ በትግሉም በአመራሩም ረጅም ግዜ የቆዩ እንዲያውም ጡረታ መውጣት የነበረባቸው ሰው ናቸው:: በአማራ ክልል የጤና ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ራዲዮ እና ቴሌቪዥን ድርጅት እና በኢፌዴሪ የፍትህ ሚኒስቴር ውስጥ በደምብ የሚታወቁ ሰው ናቸው:: አቶ አያሌው ጎበዜ የክልሉ ፕሬዚዳንት ሆነው ላለፉት 5 ዓመታት አገልግለዋል:: የአቶ አዲሱ ለገሠን እንኳ ሁሉም ያውቃል:: እንለፋቸው:: አቶ ብናልፍ አንዱዓለም ለማእከላዊ ኮሚቴው አዲስ ባይሆኑም ለስራ አስፈፃሚው ግን አዲስ በመሆናቸው የሳቸውን መምጣት እንደ ልዩ ክስተት ማየት ይቻላል:: ከዚህ ሌላ አዲስ ሊባሉ የሚችሉት አቶ ደመቀ መኮንን እና አቶ ገዱ አንዳርጋቸው ናቸው:: አቶ ደመቀ መኮንን አመጣጣቸው በ 1980ዎቹ መጨረሻ ቢሆንም በተለይ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ትርጉምም ሆነ የኢህአዴግ የፖሊሲ ምንነት ከልብ ማርኳቸውና ገብቷቸው ሳይሆን ከአሰልቺው የኬሚስትሪ መምህርነት ሞያቸው ወጥተው ሲያማትሩ ያገኙት ዳጎስ ያለ ጥቅምን የሚያስገኝ ነገር በመሆኑ ነው ንቅናቄውን የተቀላቀሉት:: በምርጫ 2002 ክርክር ካንዴም ሁለቴ ቀርበው በሕዝብ እንዲታዩ የተደረጉ ናቸው:: ኢህአዴግ ከብአዴን ትልቅ ፈተና በተለይ በቀድሞው የትምህርት ሚኒስትር በዶ/ር ስንታየሁ ኃ/ሚካኤል ሲመጣበት አሁንም ከብአዴን አቶ ደመቀን በማስቀመጥ ሊወጣው ሞክሯል:: እናም ላለፉት 3 ያህል አመታት በሚኒስትርነት ቢያገለግሉም ብዙ ሕዝብ አያውቃቸውም ልንል እንችል ይሆናል:: ከዚህ

በተጨማሪ በትጥቅ ትግሉ አልነበሩም፡፡ አቶ ገዱ አንዳርጋቸው ከጥቂት ወራት በፊት የአማራ አቀፍ ልማት ማኅበር (አልማ) እጅግ የተሳካለት ቴሌቶን አካሂዶ በብዙ ሚልዮኖች የሚቆጠር ብር ገቢ ሲያደርግ በብዙዎች ዘንድ «ይኼ የገዱ ሥራ ነው፤» የተባለላቸው ሲሆኑ ለብአዴን ማእከላዊ ኮሚቴ አዲስ ባይሆኑም አሁን ግን ወደ ላይኛው አመራር ሲመጡ አዲስ ፊት ናቸው ሊባሉ ይችላሉ፡፡ እንዲያውም ነሐሴን ወር በሙሉ ድፍን ባሕር ዳር፤ «ገዱን የክልሉ ፕሬዚዳንት ያደርጉታል» የሚሉ ወሬዎች በርክተው ነበረ፡፡ ታዋቂ ምንጮቼ ግን ከአቶ አያሌው እጅ አሁንም የክልል ፕሬዚዳንትነቱ እንደማይወጣ ይከራከራሉ፡፡

በመቀጠል የምናልፈው በኢህአዴግ ውስጥ የሶስተኛ ደረጃ ኖሮት ለረጅም ግዜ ወደቆየውና ሙሉ በሙሉ ማለት በሚቻል ሁኔታ በብቃት የለሽ አጎብዳጆች ወደተዋቀረው የኦሮሞ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ድርጅት (ኦህዴድ) ነው፡፡ የኦህዴድ ማዕከላዊ ኮሚቴ እና ከዚያም አነስ ባሉ መዋቅሮች ያሉ አባላት በአዳማ ከተማ በ2002 መጨረሻ ከሚደረገው ስብሰባ በፊት ቀደም ብሎ በግምገማ ስለሚመቱ ሰዎች ተነገራቸው፡፡ ከዚያም አፈ-ቀላጤ የሆኑ ሰዎች ተነስተው በመድረክ መሪው የተጠና እና ስልታዊ ዕድል አሰጣጥ እነዚህን ሰዎች ለሰይጣን እንኳ በማይመኙት ክፉ ቃልና አነጋገር እንዲቀጠቅጧቸው ተደረገ፡፡ ግን የሚያሳዝነው ዋና ዋና አጥፊዎቹ ቁጭ ብለው ይኼ ሁሉ ውርጅብኝ በትናንሾቹ ላይ ብቻ እንዲወርድ የተደረገ መሆኑ ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ ተጠያቂው አጎብዳጁ ኦህዴድ ከዚያ ደግሞ ይኼንን ያቀነባበረው ሕወሓት ነው፡፡



*ከግራ ወደ ቀኝ አቶ ዘላለም ጀማነህ የኦህዴድ ጽ/ቤት ኃላፊ*


*እና አቶ ሙክታር ከድር የኢህአዴግ ጽ/ቤት ኃላፊ*

ቀደም ብዬ እንደገለጽኩት በዚህ ስብሰባ ላይ በምስጢር ድምጽ አሰጣጥ ሂደት የስብሰባው ተሳታፊዎች 65 ያህል አባላት ያሉትን የማዕከላዊ ኮሚቴ መረጡ፡፡ ከእነዚህ ውስጥም የሚከተሉትን 9 አመራር አባላት ኦሕዴድን ወክለው በኢህአዴግ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ውስጥ እንዲገቡ ወሰኑ፡፡

1. አቶ ዓለማየሁ አቶምሣ
2. አቶ ሙክታር ከድር
3. አቶ ኩማ ደመቅሣ
4. አቶ ሱፍያን አህመድ
5. አቶ አባዱላ ገመዳ
6. አቶ ግርማ ብሩ
7. አቶ ዘላለም ጀማነህ
8. አቶ አብዱላዚዝ መሐመድ
9. አቶ ድሪባ ኩማ

ስለ «መተካካት» ብዙ ቢወራም ኦህዴድ ግን ለኢህአዴግ ሥራ አስፈፃሚነት እንዲወክሉት ባስመረጣቸው በነዚህ 9 ብዙ የምናውቃቸው አሮጌ ፊቶች ብቻም ሳይሆን በ 65 ያህል

የማዕከላዊ ኮሚቴ አባላቱም ምርጫ ብዙም አዳዲስ ፊቶችን የማያመጣ፤ «መተካካት» የሚባለው ነገርም ብዙ አጀንዳው እንዳልሆነ በገሀድ ያረጋገጠ ነው:: ብዙ ቀደም ብለን የምናውቃቸው ከፍተኛ አመራሮች በሁለቱም መዋቅሮች ውስጥ ትልልቅ ቦታ ይዘው እንደሚቀጥሉ ምርጫው ይፋ አድርጓል:: በድብቅ 56 ገጽ የሚሆን አረመኔያዊ ጭፍጨፋ-መሰል ግምገማ በጠ/ሚኒስትሩ በሚመሩ ባለሟሎች ተዘጋጅቶባቸው እንደነበረ የተነገረላቸው አቶ ኩማ ደመቅሣ በሁለቱም ኮሚቴዎች ውስጥ ጥሩ ቦታን ማግኘት ችለዋል:: ኢህአዴግ ገና ለሚቀጥሉት 2 ዓመታት ያህል በሚዘልቀው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ውስጥ ለዚያውም ከንቲባ ሆኖ ያለን ሰው ለምን አሁን ይቀጠቅጣል? ግን በመቀስ ሪቫን ከመቁረጥ በቀር ለከተማዋ ዕድገት አንዳችም አስተዋጾ ማድረግ ያቃታቸው ኩማ አንድ ቀን ጉዳቸው እንደሚፈላ ፈርተው እንዲቆዩ ለማድረግ የታሰበ ይመስላል:: አቶ ጁኔይዲ ሳዶ ምንም እንኳ ከሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ቢወጡም በማዕከላዊ ኮሚቴ ውስጥ ግን 40ኛ ሆነው ተመርጠዋል::



*ከግራ ወደ ቀኝ አቶ ግርማ ብሩ፤ አቶ ሱፍያን አህመድ፤ አቶ አባዱላ ገመዳ እና አቶ ኩማ ደመቅሣ*

አቶ ሱፍያን አህመድ እጅግ በጣም የቆዩ የረጅም ግዜ የኢህአዴግና የኦህዴድ አባል ናቸው:: የሳቸው ዳግም ምርጫም ኢህአዴግ ኢትዮጵያ በምትመራበት የፓርላሜንታዊ ሥርዓት መሠረት ጠ/ሚኒስትሩ ከሁለት ሳምንታት በኋላ ይፋ እንደሚያደርጉት በሚጠበቀው የሚኒስትሮች ም/ቤት ውስጥ ቀደም ሲል የያዙትን ቦታ እንደማይለቁ ያመላከተ ነው:: አቶ አባዱላ ገመዳ ነባር የኦህዴድና የኢህአዴግ አመራር አባል ሲሆኑ አጉል ከገዘፈው ሰውነታቸው፤ ከጅላጅል አነጋገራቸውና የተባሉትን ለመፈፀም የቱንም ያህል ርቀት ያለ ሐፍረት ከመሄድ ሚናቸው ባሻገር «አባዱላን ያህል ኦሮሞን የከዳ ማን አለ?» እስከመባል የደረሱ ቱባ በሙስናውም፤ በስልጣን ጥመኝነቱም በጥገኝነቱም ባሕር እስኪበቃቸው የዋኙ ግን ኢህአዴግን ስለማይከዱ እንዲያውም ክልሉን ለቅቀው በፌዴራል ደረጃ ስልጣን እንዲያገኙ የታጩ ሰው ናቸው:: ከ 2 ሳምንታት በኋላ ይፋ በሚደረገው የስልጣን ድልድል መሠረት አንዳንዶች ም/ጠ/ሚኒስትር ይሆናሉ ሲሉ ሌሎች ደግሞ በሚኒስትርነት ማእረግ የጠ/ሚኒስትሩ ከፍተኛ አማካሪ በመሆን ይሾማሉ ይላሉ:: አቶ ግርማ ብሩ? ማንም ያውቃል

እንለፍና እንሂድ፡፡ አቶ ዘላለም ጀማነህን አብዛኛው ሕዝብ ያውቃቸዋል፡፡ ለፓርቲው ፈጽሞ አዲስ ምልምልም ሆነ ፊት አይደሉም፡፡ እንዲያውም በስልጣን ሹምሽሩና ግምገማው ቀላል የማይባል ሚና ይዘው የዘለቁ ሰው ናቸው፡፡ መልካቸውን ያሳመሩት አቶ ዘላለም እስከ አሁን ድረስም የኦህዴድ ጽ/ቤት ኃለፊ ሆነው እያገለገሉ ነው፡፡ አቶ ሙክታር ከድር ምናልባት አዲስ ልንላቸው ብንችልም የኢትዮጵያን የፖለቲካ ሁኔታ ለሚከታተሉ ግን ከ 2000 ጀምሮ አሉ፡፡ የኢህአዴግ ጽ/ቤት ኃላፊነት ያህል የተሸከሙ ቃል አቀባይ በመሆን ያገለገሉ ሰውን ሕዝብ ሊረሳ አይችልም፡፡ አቶ አብዱላዚዝ መሐመድ የድሬዳዋ ከተማ ከንቲባ ሆነው ነበረ አብዛኞቻችን የምናውቃቸው፡፡ አሁን ደግሞ ወደ ኦህዴድ መዋቅር ውስጥ ዘልቀው በመግባት ላይ ያሉ ሰው ናቸው፡፡ አዲስ ፊት ሊሆኑ ከቶም አይችሉም፡፡ አቶ ድሪባ ኩማም ለኦህዴድ እንዲሁ አዲስ የሚባሉ ፊት አይደሉም፡፡ ነገር ግን በተለይ ከቅርብ ግዜ ጀምሮ ወደ ሕዝብ እንዲወጡ ተደርጓል፡፡ በምርጫ 2002 ነጭ ካፒታሊዝምን ከአብዮታዊ ዴሞክራሲ ጋር በግድ ሊያመሳስሉ ሞክረው የማይሆን ጨዋታ ጀምረው በአቶ ልደቱ አያሌው ክፉኛ የተረቱ ማፈሪያ መሆናቸውን አገር ያውቃል፡፡ ሊቀመንበር ሆነው የተመረጡት አቶ ዓለማየሁ አቶምሣ ምናልባት በአዲስነት ሊታዩ ይችላሉ፡፡ «ስስ ካድሬ» ባይባሉም መሠረታዊ የሚባሉ አይዲኦሎጂያዊ ጉዳዮችን በጥልቀት የመረዳት ችሎታቸው ላይ ብዙዎች ጥያቄ ያነሳሉ፡፡ የገዢው ፓርቲ ካድሬዎች ማሰልጠኛ በሆነው በሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ የሕግ ዲግሪ ካገኙ በኋላ ወደ ቻይና በሕዝብ ፖሊሲ የማስትሬት ዲግሪ ለመስራት ሄደው ነበረ፡፡ በኢትዮጵያ ራዲዮ እና ቴሌቪዥን የነበራቸውን የዳይሬክቶሬትነት ሚና ባለመውደዳቸው ወደ ኦሮሚያ ክልል የሕዝብ ግንኙነት ሄደዋል፡፡

እንግዲህ የሚቀረን እስከ አሁን በነበረው ሁኔታ በኢህአዴግ ውስጥ መጨረሻ ተደርጎ የሚታየው ነገር ግን «በኋላ የመጣ. . .» እንዲሉ የም/ሊቀመንበርነቱን ቦታ የያዘው ምናልባትም የም/ጠ/ሚኒስትርነቱን ቦታም ሊያገኝ የሚችለው የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ደኢሕዴን) ነው፡፡ የደኢሕዴን ምክር ቤት አባላት የኢህአዴግ ደምብ በሚያዘው መሠረት የብሔር ብሔረሰቦች መናኸሪያ በሆነችው ተወዳጇ የሐዋሣ ከተማ

ከጳጉሜን 3 ጀምረው መደበኛ ጉባዔያቸውን በማካሄድ 65 አባላት ያሉትን የማዕከላዊ ኮሚቴ ከከፍተኛ እና ኃይለኛ ግምገማ በኋላ አካሄደ። በዚህ ስብሰባ ላይም በብአዴን እንደተመለከትነው በክልሉ የጤና እና የትምህርት ቢሮዎች ውስጥ ሆነው በቆዩባቸው ባለፉት 5 ዓመታት ፈጽመዋል በተባሉባቸው የተለያዩ ጥፋቶች የተገመገሙ አባላቱ አንዳንዶቹ ከማዕከላዊ ኮሚቴው የመሸቀንጠር፤ ሌሎች በቀረበባቸው የሰው፤ የሰነድም ሆነ ሌላ ማስረጃ እጅግ ወደ ለየለት የሙስና ቅሌት ውስጥ መግባታቸው የተረጋገጠባቸው አባላት ግን እድሜ ከ «ኮር» አባላቱ ጋር ለፈጠሩት የጥቅም እና የ «አልነካህም፤ አትንካኝ» ሰንሰለት አለቃቅሰውም ቢሆን በስተመጨረሻ የማእከላዊ ኮሚቴ አባልነታቸውን እንዲይዙ ተደርጓል። ለምሳሌም ጳጉሜን 4 ላይ ከተደረገው ምርጫ ጥቂት ቀደም ብሎ ግምገማ ላይ በክልሉ የትምህርት ቢሮ ውስጥ ረዘም ላለ ግዜ ያገለገሉት የደኢሕዴን እና የኢህአዴግ አባላት አቶ ጣሰው ገብሬ እና ወ/ሮ ሙፍሪሀት ካሚል ላይ የሰላ ሂስ ተሰነዘረ። የፕሬዚዲየሙ መሪ አም/ር ተሾመ ቶጋ እድሉን የሰጧቸው ካድሬዎች አቶ ጣሰውን፤

«ቆምኩለት ለሚለው ዓላማ ባለው ጽናት ላይ እንደ ሶፍት ቀልሎ የሚታይ፤»

«ለአባላት በሚያሳየው ንቀት ብዙዎችን ያማረረ፤»

«በመንግሥት የሥራ ሰዓት በየሺሻ ቤቱ የሚገኝ፤»

«በቢሮው የተንሰራፋውን ምዝበራ ለማቆም አንዳችም ተነሳሽነት እና ጥረት ያላደረገ፤»

በማለት ክፉኛ ወረዱባቸው። ወ/ሮ ሙፍሪሀትን ደግሞ፤

«እሷ በኃላፊነት በተጎለተችበት ቢሮ ትምህርት ተቃዋሚዎች እንዳሉት ወደ ዝቅጠት ሊያመራ ምንም አልቀረውም፤»

«ቁርጠኝነትን እና የብቃት ማረጋገጫን የመሳሰሉ መመዘኛዎችን ላላሟሉ አባላት የነፃ ትምህርት ዕድል እንደ ቀበሌ ዳቦ ያደለች፤»

«ሕዝቡና ደኢሕዴን የቆሙለትን የሰለጠነ እና መልካም ሥነ-ምግባር ያለው የሰው ኃይል የማፍራት ሂደት በግልጽ ለግል ጥቅሟ ስትል ያደናቀፈች፤»

በማለት ያዙኝ ልቀቁኝ ብለው ተውረገረጉባቸው:: ግና ምን ያደርጋል? ወ/ሮ ሙፍሪሀት ግን ከአቶ ኃ/ማርያም ደሣለኝ ጥሩ ድጋፍ ተቸራቸውና ለማዕከላዊ ኮሚቴው ከአጭር ተግሳጽ በኋላ ተመረጡ:: የደኢሕዴን አባላት በመቀጠል ከ 65 ያህሉ የማዕከላዊ ኮሚቴ ተመራጮቻቸው ውስጥ 9 አባላትን ንቅናቄውን ወክለው በኢህአዴግ ሥራ አስፈፃሚነት እንዲሳተፉ በአብላጫ ድምጽ መርጠዋቸዋል:: እነዚህም፤

1. አምባሣደር ተሾመ ቶጋ
2. አቶ ኃ/ማርያም ደሣለኝ
3. አቶ ሽፈራው ሽጉጤ
4. አቶ ሬድዋን ሁሤን
5. አቶ መኩሪያ ኃይሌ
6. አቶ ዓለማየሁ አሰፋ
7. ዶ/ር ሽፈራው ተ/ማርያም
8. አቶ ደበበ አበራ
9. አቶ ታገሠ ጫፎ

ናቸው:: ቀደም ሲል በሌሎቹ እንዳደረግነው እነዚህንም ጠልቀን እንፈትሻቸው:: ደኢሕዴን በርካታ ታዋቂ የአመራር አባላቱን በድጋሚ ለሥራ አስፈፃሚነት አስመርጧል:: ከእነዚህ መሀከልም አምባሳደር ተሾመ ቶጋ እና አቶ ኃ/ማርያም ደሣለኝ ይገኙበታል:: አምባሣደር ተሾመ ምንም እንኳ ምሁር ቢሆኑም በማጎብደድና ለራሳቸውም በደምብ ያልገባቸውን ሌሎች ላይ በመጫን የሚታወቁ ነባር አመራር አባል ናቸው:: ከ 1998 በፊት የወጣቶችና ስፖርት ጉዳይ ሚኒስቴር ሚኒስትር ነበሩ:: ከ 1998 በኋላ ብዙዎቻችን በደምብ እንደምናውቀው የኢህአዴግን የይስሙላ ፓርላማ በጠነከረ ፈርጣማ ጠማማነት እና አምባገነንነት ላለፉት 5 ዓመታት በአፈ-ጉባኤነት መርተዋል::



*ከግራ ወደ ቀኝ አምባ. ተሾመ ቶጋ፤ አቶ ሬድዋን ሁሴን፤ አቶ ሺፈራው ሽጉጤ እና አቶ መኩሪያ ኃይሌ*

አቶ ኃ/ማርያም ደሣለኝ በተለይም ከ 1994ቱ አስከፊ የሀዋሣ ጭፍጨፋ በኋላ የሲዳማን ሕዝብ ለማግለል በተደረገው ጥረት ወደ ሥልጣን የመጡ የክልሉ ር/መስተዳድር ሆነው የቆዩ፤ በመቀጠልም ላለፉት 4 ዓመታት በጠ/ሚኒስትሩ ቢሮ በሚኒስትርነት ማዕረግ ከፍተኛ አማካሪ፤ እንዲሁም ከ 2000 ዓ.ም ጀምሮ ደግሞ በሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት የመንግሥት ልዩ ተጠሪ በመሆን የቆዩ ናቸው:: አቶ ሽፈራው ሽጉጤ ጠ/ሚኒስትሩ ከአስደንጋጩ ምርጫ 97 በኋላ ምርጫው ባይጭበረበር ኖሮ በሲዳማ ዞን አሸናፊ ሊሆን ይችል ከነበረው ከሲዳማ አርነት ንቅናቄ (ሲአን) ደጋፊዎች የሲዳማ ሕዝብ  የክልልነት ጥያቄ ገፍቶ ሲመጣባቸው ባደረጉት ማቀያየር አቶ ኃ/ማርያምን አንስተው የሲዳማን ሕዝብ መደለል የሚችሉ መስሏቸው ያመጧቸው እስከ አሁንም የክልሉ ፕሬዚዳንት ናቸው:: አቶ ሬድዋን ሁሴን የፖለቲካ ትግሉን ከ 1992 ጀምሮ በተቃዋሚነት የተቀላቀሉ ሲሆኑ የስልጢ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ድርጅት (ስሕዴድ) ያስገኘላቸውን የፓርላማ ወንበር በመተው የስልጢ ሕዝብ የዞንነት ጥያቄ ሲመለስ ደኢሕዴንን የተቀላቀሉ ናቸው:: በማእረግ የባዮሎጂ ተመራቂው አቶ ሬድዋን እስከ 2000 ዓ.ም ድረስ ግን በሕዝብ የማይታወቁ በመሆናቸው፤ እንዲሁም ወደ ንቅናቄው አመራር ሲመጡ የመጀመሪያቸው በመሆኑ እንደ አዲስ አመራር አባል ልንወስዳቸው እንችላለን ባይ ነኝ:: የአዲስ አበባ የኢህአዴግ ጽ/ቤት ኃላፊ በመሆን እያገለገሉ ይገኛሉ:: አቶ መኩሪያ ኃይሌ ግን ነባር ከሚባሉ የንቅናቄው አመራር አባላት መሀከል ሲሆኑ ከአካባቢና ማሚያ ምርጫ 2000 በኋላ በተመሠረተው የአሁኑ የአዲስ አበባ አስተዳደር ውስጥ የሥራ አስኪያጅነት ማእረግ ይዘው ይገኛሉ:: አቶ ዓለማየሁ አሰፋ ከ 1998 ጀምሮ የደኢሕዴን ጽ/ቤት ኃላፊ በመሆናቸው የሚታወቁ አመራር ናቸው:: ዶ/ር ሽፈራው ተ/ማርያምን ብዙ ሕዝብ የሚያውቃቸው ይመስለኛል:: የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስትር ናቸው:: አቶ ደበበ አበራም ቢያንስ በክልሉ ሕዝብ በሚገባ የሚታወቁ ናቸው:: የክልሉ የፀረ ሙስና ቢሮ ኃላፊ ናቸው:: አቶ ታገሠ ጫፎ ደግሞ የክልሉ ምክትል ር/መስተዳድር በመሆናቸው በጣም የሚታወቁ ነባር አመራር ናቸው::

እንግዲህ ባጠቃላይ ስንመለከተው ኢህአዴግ ለሥራ አስፈፃሚነት ከአራቱ አባል ፓርቲዎቹ የተውጣጡ 36 ያህል አባላትን ይዟል:: ከእነዚህ ውስጥ ግን 12ቱ ብቻ አዳዲስ ሲሆኑ ቀሪዎቹ እና በመቶኛ ስናስቀምጣቸው 78% የሚሆኑት ግን ነባር እና የነበራቸውን ስልጣን መልሰው የያዙ አባላት ናቸው:: እናም በዚህ ዓይነቱ «መተካካት» ተብሎ ብዙ በተወራለት ድራማ ያየነው ነገር ቢኖር ጥቂት ማቀያየሮችን እና እጅግ በጣት የሚቆጠሩ አዲስ ፊቶችን ነው::

## ማጠቃለያ

ኢህአዴግ መተካካትን የሚቀበልና የሚያምን ቡድን አይደለም:: ግንባሩ ስልጣንን በእጁ ካስገባበት ከ 1983 ዓ.ም ጀምሮ በተለያዩ መዋቅሮቹ ከፍተኛ የአመራር አባላቱን ለአንድ ሰውና ለጥቂት ጭፍሮቹ ታማኝ እስከሆኑ ድረስ ለረጅም ግዜ አቅፎ ይዞ መሄድን የመረጠ ነው:: አንዳንድ ከፍተኛ ባለስልጣናቱ በዕድሜ እጅግ የገፉ እና ካለባቸው የጤና መቃወስ የተነሳ ብዙ መቆየት የማይገባቸው ቢሆንም እነዚህንም ግን ይዞ ሊቀጥል ሞክሯል:: አሁን በስተመጨረሻም ከራሱ አባላት ጭምር እነዚህን እንዲተካ ጥሪ ሲቀርብለት ያንን በተወሰነ ደረጃ ሊቀይር ሞክሯል::

ከግንባሩ ጋር መቀጠል እንደሌለባቸው ተወስኖባቸው ነገር ግን ራሳቸው በይፋ፤ «በቃኝ» እንዲሉ ከተደረጉ አመራሮች መሀከል በትጥቅ ትግሉ ዘመን ከፍተኛ ተጋድሎን ያደረጉት አቶ ተፈራ ዋልዋ ይገኙበታል:: አቶ ተፈራ ከ 3 ዓመታት በፊት በሐዋሣ ከተማ ላይ በተደረገውና ጠ/ሚኒስትሩ በመሩት የኢህአዴግ ስብሰባ ላይ የለውጥ ሂደት ሐሳብን በማራመድ ታላቅ ድንጋጤን የፈጠሩ ሲሆኑ ኢህአዴግ ያንን ሐሳብ በወቅቱ ባይቀበልም እሳቸውን ገሸሽ ካደረገ በኋላ ግን ልክ ራሱ ያመጣው አስመስሎ ተግብሮታል:: ከዚያ በኋላ አቶ ተፈራ በቋፍ ያሉ ሲሆን «እንኳንም ዘንቦብሽ. . .» እንዲሉ በመጋቢት ወር 2001 ዓ.ም. በአሜሪካ ከሚገኘው የግንቦት 7 ለነፃነትና ለዴሞክራሲ ንቅናቄ ጋራ በተላከከው «መፈንቅለ መንግስት» የሚል የብአዴንን ታማኝ ያልሆኑ አባላትና ጄኔራሎች መምቻ ዘመቻ በኋላ ሚናቸው ጭራሽ እየደበዘዘ መጥቷል:: በዚህ ዘመቻም የገዛ ባለቤታቸው አባት የሆኑት አቶ ጽጌ ኃ/ማርያም ለከፍተኛ ስቃይና ለዕድሜ ልክ እስር ከተዳረጉ በኋላ አቶ ተፈራ ታማኝ የኢህአዴግ አመራር ሊባሉ የሚችሉ መሆናቸው ላይ በራሱ በኢህአዴግ አመራሮች ዘንድ ጥርጣሬ አለ::

ከዚህ ጋር አያይዘን ልናነሳ የሚገባው በመግቢያዬ ላይ የጠቀስኩትን እና የ «መተካካት» ድራማ ውጤት የሆነው የብአዴን ሚና መቀየር ነው። እስከ አሁን በነበረው ሁኔታ ብአዴን ታኮ በመሆን ከ አራቱ ፓርቲዎች ሁለተኛውን ቀዳሚነት ስፍራ ይዞ ቆይቷል። ከአሳዛኙ የግንቦት 7 «መፈንቅለ መንግሥት» ድራማ በኋላ ግን የብአዴን አባላት ኢህአዴግን ላንዴና ለመጨረሻ ግዜ «በቃኝ!» እንዲሉ ጥሪ ቢቀርብላቸውም ምርጫ 2002ን በማጭበርበር አሁንም በድጋሚ የም/ጠ/ሚኒስትርነት እና የታኮነት ሚና የሚያገኙ መስሏቸው ዳከሩ። የጠ/ሚኒስትሩን አደገኛ ጨዋታ መረዳት ያቃታቸው ብአዴኖችም የጃቸውን አግኝተዋል። ጠ/ሚኒስትሩ በርካቶች እንደሚያምኑት በገዛ ፓርቲያቸው ውስጥ በአገሪቱ እጅግ አብላጫ ቁጥር የያዙትን የአማራ እና የኦሮሞ ብሔር ተወላጆችን «እንወክላለን» የሚሉት ሁለቱ ድርጅቶች (ብአዴን እና ኦሕዴድ) ወደ ፓርቲው ሊቀመንበርነትም ሆነ ወደ ጠ/ሚኒስትርነት ለመምጣት የሚያደርጉትን ፍትጊያ እስከ አሁን በነበረው ሁኔታ ብአዴንን ደግፎ ኦህዴድን በማሳፈር እና ከተቻለም ሁለቱን በማጣላት ሊያልፉት የሞከሩ ሲሆን ዘንድሮ በቆመሩት ቁማር ስሌት ግን ብአዴንን ጭራሽ ቆሌውን በመግፈፍ ኦህዴድን ደግሞ አቋምጦ ወዲያው ላልተጠበቀው ደኢህዴን የምክትልነት ሚናውን መስጠት ነው። ይኼ ያልተጠበቀው የ «መተካካት» ውጤት ነው።

በሚቀጥሉት አምስት አመታትም ከኢህአዴግ ወደ ሥልጣን መምጣት ጀምሮ በጥቂቱም ቢሆን ደፍሮ የሕወሓት የበላይነትን ለመቃወም በሞከረው በብአዴን እና ለዚህ የሚሆን ወኔም ሆነ ሐሞት አላቸው ብሎ ለመናገር በሚያስቸግሩት ኦህዴዶች መሀከል የሚቀጥለውን ጠ/ሚኒስትርነት ቦታ ለማግኘት የሚደረግ ፍትጊያ እንዲኖር ብልሁ ጠ/ሚኒስትር መሬቱን አመቻችተዋል። በዚህ ግጭትም የፓርቲው ግምገማ ከአባል ፓርቲዎች ወጥቶ በኢህአዴግ ደረጃ እንዲካሄድ የሚደረግ ሲሆን ታዋቂ ምንጮች እንደሚሉት ደግሞ ኢህአዴግ ሙሉ በሙሉ ኮረጆ ገልብጦ በድርቅና 99.63% አገኘሁ በሚልበት ፓርላማ ውስጥም በሁለቱ መሀከል በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ ትግል ሊደረግ ይችላል። ከአሽከርነት እና ከተለጣፊት የዘለለው ሚና እንደ ሰማይ መና የራቃቸው እና ባዕድ የሆነባቸው ደኢሕዴኖች ደግሞ ሳያስቡት በሎተሪ የመጣላቸውን የም/ጠ/ሚኒስትርም ይሁን የም/ሊቀመንበርነት ሚና እንደያዙ ለመቆየት ሲሉ ከሚገባው በላይ ለጠ/ሚኒስትሩ እና ለሕወሓት ታማኝ ሆነው ይቆያሉ።

በሌላ በኩል 36 አባላት ካሉት የኢህአዴግ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ መሀከል ኢህአዴግ ቆምኩለት እያለ የሚለፍፈው የሴቶችን ማበረታታት ፋከራ ውሸት መሆኑን ባረጋገጠ መልኩ አንድ ሴት አባል ብቻ አለ። ይኼ ሁሉ የሥራ አስፈፃሚው ስብጥር እንደሚያመለክተው ከሆነም ከመበስበስ ያልዳነው የኢህአዴግ አመራር ምንም ተተኪ አመራር ለማዘጋጀት

እንዳልቻለ እና እነዚህኑ ይዞ በመንገታገት በግምት አገሪቱን እንደምንም ለመምራት እንደሚያስብ ነው::

**በመጨረሻም**

↓




**አቶ አህመድ አባጊሣ አባኡርጌሣ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ (መድረክ) የአዲስ አበባ አስተዳደር ከፍተኛ አደራጅ አባል ናቸው:: ለአስተያየቶቻችሁና ጥያቄዎቻችሁ በ ahmedgissa232@gmail.com ልታገኟቸው ትችላላችሁ::**